ከአለርት ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል
ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም

# በኢትዮጵያ ጤናማ ሕብረተሰብን ለመፍጠር የአለርት ሚና

**ዳንኤል ዘነበ**

ሁሉም ኢትዮጵያዊ የጤና አገልግሎት ማግኘት እንዳለበት ኢትዮጵያ ከተቀበለቻቸው ዓለም አቀፍ የሠብዓዊ መብቶች አንዱ እንደሆነ ይታወቃል። ይህንንም ሀገሪቱ የሕጓ አካል አድርጋ በፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት በተለያዩ አንቀፆች ደንግጋለች። በዚህም መሠረት በአንቀፅ 90 ንኡስ አንቀፅ 1 “የሀገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ሁሉም ኢትዮጵያዊ የትምህርት፣ የጤና አገልግሎት፣ የንፁሕ ውሃ፣ የመኖርያ፣ የምግብና የማህበራዊ ዋስትና እንዲኖረው ይደረጋል” ሲል የደነገገ ሲሆን በአንቀፅ 92 ንኡስ አንቀፅ 1 ደግሞ መንግሥት ሁሉም ኢትዮጵያዊ ንፁሕና ጤናማ አካባቢ እንዲኖረው የመጣር ኃላፊነት እንዳለው በግልፅ ተደንግጓል ።

በተጨማሪም በሕገ መንግሥቱ አንቀፅ 35 ንኡስ አንቀፅ 9 ሴቶች በእርግዝናና በወሊድ ምክንያት የሚደርስባቸውን ጉዳት ለመከላከልና ጤንነታቸውን ለማስጠበቅ የሚያስችል መብት አስቀምጧል። እንዲሁም በአንቀፅ 36 ንኡስ አንቀፅ 1 ስለ ህፃናት በሕይወት የመኖር እና ጤንነት መጠበቅን ይደነግጋል። በአንቀፅ 44 ንኡስ አንቀፅ 1 ደግሞ ሁሉም ሰዎች ንፁሕና ጤናማ በሆነ አካባቢ የመኖር መብት እንዳላቸው ይጠቅሳል ።

ስለሆነም በሕገ መንግሥቱ ድንጋጌዎች መሠረት እያንዳንዱ ዜጋ የጤና አገልግሎት የማግኘት መብት ተግባራዊ ለማድረግ ይቻል ዘንድ መንግሥት የጤና ፖሊሲ በመቅረፅና ስትራቴጂዎችን በመንደፍ መብቶቹ እንዲጠበቁ ያደርጋል። ከዚህ አንጻር ኢትዮጵያ የሕገ መንግሥት ድንጋጌዎች መሠረት ያደረገ የጤና ፖሊሲን ተግባራዊ እያደረገች ነው። ባለፉት ዓመታት የጤና አገልግሎት ሥርዓቱን ለማጠናከር ሰፋፊ ሥራዎች ተሠርተዋል። በርካታ የጤና ተቋማት በመገንባትና የጤና ባለሙያዎች አሰልጥኖ በሥራ ላይ እንዲሠማሩ በማድረግ በመሠረታዊ ጤና አገልግሎት ሽፋን ላይ አመርቂ ውጤት ማስመዝገብ እንደተቻለ ይታወቃል።

ለዚህ ሀገራዊ ስኬት እንደ አለርት ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ያሉ አንጋፋ የጤና ተቋማት ከፍተኛ ሚና አላቸው። አለርት በሀገራችን ቀደም ካሉ ጊዜያት ጀምሮ ከስጋ ደዌ ጋር ለተያያዙ የጤና ችግሮች መፍትሔ በመስጠት ይታወቃል። በአፍሪካ አህጉርም በጤናው ዘርፍ ስሙ የገነነ፤ በብዙ ኢትዮጵያውያን ልብና አዕምሮ ውስጥ ዘወትር የሚታወስ ተቋም ጭምር ነው።

እ. ኤ. አ በ1922 በቀዳማዊ አፄ ኃዳማዊሥላሴ የተመሠረተው አለርት ሆስፒታል ከቆዳ እና ስጋ ደዌ ሕመም ጋር ተያይዞ ማከሚያ፣ ማስተማሪያና የማገገሚያ አገልግሎት ለመስጠት በሚል እንደተቋቋመ መረጃዎች ይጠቁማሉ። አለርት በአፍሪካ የመጀመሪያው የሥጋ ደዌ፣ የሳንባ ነቀርሳ እና ማገገሚያ ማሠልጠኛ ማዕከል በመሆን ሲያገለግል ቆይቷል። በአሁኑ ወቅት ከማዕከልነት ወደ ሁሉን አቀፍ አገልግሎት በመሸጋገር ኮምፕርሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል ለመሆን በቅቷል ።

ሆስፒታሉ አጠቃላይ የሕክምና አገልግሎቶች ማለትም የፕላስቲክ እና ሪኮንስትራክቲቭ ቀዶ ጥገና ሕክምና፣ የአጥንት ቀዶ ጥገና ሕክምና፣ የቆዳና የአባላዘር ሕክምና፣ የድንገተኛ እና ፅኑ ሕሙማን ሕክምና፣ የእናቶችና የጨቅላ ሕጻናት ሕክምና፣ የጠቅላላ ቀዶ ጥገና ሕክምና፣ የሕፃናት ሕክምና፣ የውስጥ ደዌ ሕክምና፣ የጥርስ ሕክምና፣ የአይን ሕክምና እና የሥነ - አዕምሮ ሕክምና እየሰጠ ይገኛል። ሆስፒታሉ የጤና ማበልፀግንና በሽታ መከላከልን በማስፋትና በማጠናከር በማህበረሰብ ጤና ረገድ ስኬታማ ሥራዎችን መሥራት እንደቻለ መረጃዎች ያመለክታሉ።



ዶ/ር ቢያድግልኝ አጥናፉ ፤

የጤና ፖሊሲው ከማህበራዊና ኢኮኖሚያዊው ዕድገት ጋር የሚጣጣም፣ የህብረተሰቡን ባለቤትነት የሚያረጋግጥ ጤና ማበልጸግ እንዲገባ ያስቀምጣል። ከዚህ አኳያ አፍሪካን ያማከለ ግዙፍ ርዕይ ይዞ የተነሳው፣ የመላው አፍሪካ የሥጋ ደዌ፣ የሳንባ ነቀርሳ እና ማገገሚያ ማሠልጠኛ ማዕከል (አለርት) በሁሉም የተቋሙ የሥራ ክፍሎች በኩል በአለርት የቤተሰብ ህክምና እና የማህበረሰብ ጤና ክፍል እየሠራቸው ያሉ አመርቂ ሥራዎች ይጠቀሳሉ። ዶ/ር ቢያድግልኝ አጥናፉ በአለርት ኮምፕሪሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የቤተሰብ ህክምና እና የማህበረሰብ ጤና ክፍል ኃላፊ ናቸው ።

ዶክተር ቢያድግልኝ እንደሚሉት በጤና ፖሊሲው ጤና ማበልጸግና በሽታ መከላከል ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ እንደሆነ ይታወቃል። ዓላማውም በህብረተሰቡ ባለቤትነት የጤና ማበልፀግንና በሽታ መከላከልን በማስፋትና በማጠናከር ህብረተሰቡ የራሱን ጤና በራሱ በምልዓተ ሕዝብ ደረጃ እንዲያመርት ማድረግ ነው ።

የአለርት ሆስፒታል ቤተሰብ ህክምና እና የማህበረሰብ ጤና የሥራ ክፍልም በአጥቢያው ያሉትን ጤና ጣቢያዎችን እና ሆስፒታሎችን የሚያግዝ፣ የሚያስተምር እና የሚያበቃ የሥራ ክፍል ነው። አንድ የጤና ተቋም ማገልገል ያለበት ሆስፒታል የሚመጣውን ህብረተሰብ ብቻ አይደለም። ተቋሙ በዙሪያው ያለውን ማህበረሰብ፣ ራሱ የተቋሙ ሠራተኞችን፣ ሌሎች አቻ ተቋማትን ማገዝ እና ማገልገል ይኖርበታል። ይህን ግብ ለማሳካት የቤተሰብ ህክምና እና የማህበረሰብ ጤና ክፍል እንዲቋቋም መደረጉን አስታውቀዋል ።

ዶክተር ቢያድግልኝ ፤ ሆስፒታሉ የማህበረሰብ ጤና ላይ ትኩረት አድርጎ ሲሠራ መቆየቱን ጠቅሰው ፤ የመጀመርያ ደረጃ የጤና እንክብካቤ (Primary Health Care) ላይ ትኩረት አድርጎ በመሥራት ደረጃውን የጠበቀ የመሠረታዊ ጤና አገልግሎት ተደራሽ ለማድረግ የሚያስችሉ በርካታ ሥራዎች መሠራታቸውን ገልጸዋል ።

እንደ እርሳቸው ገለጻ ፤ በተቋሙ ከማህበረሰብ ጤና ጋር ተያይዞ በአቅም ግንባታ ላይ ብዙ አልተሠራም። ባለፉት ሦስት ዓመታት አለርት ከተለያዩ ተቋማት ጋር ትስስር በመፍጠር ውጤታማ ሥራዎች ተከናውነዋል። የጤና ተቋማቱ ባሉበት ባለሙያዎችን የማብቃት ፣ ተቋማቱ ተኝቶ ህክምና አገልግሎት እንዲሰጡ ድጋፍ የማድረግ ፣ ታካሚዎች የተመላላሽ ህክምና ተገልጋዮች በአቅራቢያቸው በሚገኝ ተቋም አገልግሎት የሚያገኙበትን መንገድ የመፍጠር ሥራዎች መሥራት ተችሏል ።

በአሁኑ ወቅት በሁለት ጤና ተቋማት ተኝቶ ህክምና አገልግሎት እንዲጀመር ተደርጓል ። ኮልፌ ቀራኒዮ ወረዳ 3 እና ወረዳ 9 ተኝቶ ህክምና አገልግሎቱ ይሰጣል። በሆስፒታሉ ታካሚዎች ሲበዙ በእነዚህ ተቋማት ተኝተው ህክምናቸውን እንዲከታተሉ ይደረጋል ። ታካሚዎች ባሉበት እንዲታከሙም ተደርጓል። ይህ ደግሞ ከዚህ በፊት ያልነበረ ነው ፤ በጤና ጣቢያ ተኝቶ ህክምና አገልግሎት የማይታሰብ ነበር። ወደ ተቋማት በመሄድ ህክምና እና የአቅም ግንባታ ትምህርቶች በአለርት አማካኝነት ይሰጣል። በተጨማሪም በአዲስ አበባ በሚገኙ 11 ጤና ጣቢያዎች ድጋፋዊ ጉብኝቶች ይደረጋል። እንደየአስፈላጊነቱ የህክምና ቁሳቁሶች ድጋፍ እና ከአገልግሎት ጋር ተያይዞ ሙያዊ እገዛዎችን ይደረጋሉ።

በዚህም አለርት የመሠረታዊ ጤና አገልግሎቱ ደረጃውን የጠበቀ፣ ፍትሀዊ በሆነ መልኩ ማድረስ እንዲቻል ፣የመጀመርያ ደረጃ የጤና እንክብካቤ (Primary Health Care) እንዲጠናከሩ በማድረግ በጤናው ዘርፍ የማይደበዝዝ ዐሻራውን ማኖር እንደቻለ አብራርተዋል ።

ከማህበረሰብ ጤና ጋር ተያይዞ የተሠራውን ሥራ በተመለከተ አያይዘው ያነሱት ዶክተር ቢያድግልኝ ፣ ከመደበኛው የህክምና አገልግሎት በተጨማሪ በተለያዩ የመንግሥትና የግል ተቋማት የሚሰጠውን ተከታታይ የሆነ ነፃ የበጎ አድራጎት የህክምና አገልግሎት መኖሩን አመላክተዋል። ባለፉት ሁለት ዓመታት በሆስፒታሉ ነፃ የህክምና አገልግሎት የሚሰጥ የበጎ አድራጎት ህክምና ቡድን በማቋቋም ለተለያዩ የማህበረሰብ አካላት አገልግሎቱን መሰጠቱን ተናግረዋል።

በ2015ዓ.ም ከ26ሺህ በላይ ለሆኑ የማህበረሰብ ክፍሎች ነጻ የህክምና ምርመራ እና የምክር አገልግሎት የተደረገ ሲሆን በ2016.ም ደግሞ ለኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ሠራተኞች ፣ ለገንዘብ ሚኒስቴር ሠራተኞች ፣ ለታላቁ ህዳሴ ግድብ ግንባታ ሕዝባዊ ተሳትፎ ማስተባባሪያ ብሄራዊ ም/ቤት ጽ/ቤት ሠራተኞች፣ ለመቄዶንያ እና ለሌሎች በርካታ ተቋማት የደም ግፊት፣ የስኳር፣ የቆዳ ፣ የዓይን፣ የጥርስ እንዲሁም የሌሎች በሽታዎች ነጻ ምርመራ እና የምክር አገልግሎት ከ77 ሺህ በላይ ለሆኑ የማህበረሰብ አካላት ነጻ የህክምና ምርመራ እና የምክር አገልግሎት መሰጠት መቻሉን አብራርተዋል ።

የክረምት ነፃ የህክምና አገልግሎቱ ተጠናክሮ የሚቀጥል ይሆናል ያሉት ዶክተር ቢያድግልኝ፣ በ2017 ዓ.ም በጀት ዓመት በነፃ የህክምና አገልግሎት የበጎ አድራጎት ሥራው በክረምት እና በበጋ በጎ ፈቃድ አገልግሎት ለ100 ሺህ ሰዎች የህክምና አገልግሎት ለመስጠት እቅድ ተይዞ እየተሠራ ይገኛል ብለዋል ።

ከጤና ዕውቀት በማበልጸግ ጋር ተያይዞ በርካታ ሥራዎች መሠራታቸውን ያመላከቱት ዶክተር ቢያድግልኝ፣ ማህበረሰቡን የጤና ትምህርት በማስተማር የጤና ዕውቀቱን ለማሳደግ ጥረት መደረጉን ገልጸዋል። በጤና ዕውቀት ማበልጸግ አገልግሎቱ በደንበኞችም ሆኑ በጤና እንክብካቤ አቅራቢዎች መካከል የተሻለ መግባባት እና ምቾት በመፍጠር የጤና ትምህርት እና ምርመራ እንቅስቃሴዎችን ለማስረዳት እና ለመተግበር የተለያዩ አካሄዶችን ይጠቀማል የሚሉት ኃላፊው ፣በሚኒ ሚዲያ ፣ፊት ለፊት ትምህርት፣ በድምጽ፣ በምስል ፣ የተለያዩ የህትመት ውጤቶች በማዘጋጀት ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ ይሠራል ።

ለአብነትም ሆስፒታሉ በጤናው ዘርፍ ለማስተማሪያና የራሱ ግብዓት የሚጠቀምበት ቁጥር አንድ የጤና እውቀት ማበልፀግ ማስተማሪያ መፅሃፍ ማስመረቅ እንደቻለ አስታውሰዋል። በመጽሀፉ ተገልጋዩ ማህበረሰብ የንባብ አድማሱን በማስፋት የተለያዩ የጤና ግንዛቤዎችን የሚያውቁበትና ከአስራ ሁለት በላይ የሆስፒታሉ ሥራ ክፍሎች ተካተውበታል። ከዚሁ ጋር ተያይዞ በሆስፒታሉ እየተከናወኑ የሚገኙ ተግባራት ለሌሎች ተቋማትም ልምድና ተሞክሮ መሆናቸውን እና የጤና ትምህርት እንደ ተቋም ለሀገር ምሳሌ በመሆን ወደፊት አንድ ደረጃ እንደሚያስኬደው ነው ዶክተር ቢያድግልኝ የተናገሩት ።

በመጨረሻም ዶክተር ቢያድግልኝ፣ አጠቃላይ በአለርት ኮምፕሪሄንሲቭ ስፔሻላይዝድ ሆስፒታል የቤተሰብ ህክምና እና የማህበረሰብ ጤና ክፍል ከተጀመረ ሦስት ዓመቱ ሲሆን እስካሁን ያለው ሂደት ጥሩ የሚባል ነው። እንደ ሆስፒታል አስፈላጊ የሚባሉ ቦታዎች ላይ እየሠራን እንገኛለን። ነገር ግን በማህበረሰብ ጤና በ11 ጤና ጣቢያዎች ነው አገልግሎቱ እየተሰጠ ያለው። እነዚህን ጤና ጣቢያዎች ለማብቃት የግብዓት እና ለተመላላሽ ህክምና የስፔሻሊቲ ህክምና ባለሙያዎች ማለትም የዓይን፣ የቆዳ እና የሥነ አእምሮ ስፔሻሊስት ሀኪሞች እጥረት ተግዳሮቶቻችን ናቸው ብለዋል።